# እልልልል. . .የሥጋ ዋጋ ወደ ብር 52 ሊወርድ ነው!

ተሻለ መንግሥቱ ( teshalem1@gmail.com)

*«መንግሥቲ አሁን ሎሕዝቡ እያሳየ ያለውን ተቆርቋሪነት ስንመለከተው ኢሕአዴግ ለሕዝቡን ያለውን ታማኝነትና ፍቅር ይገልጻል።» በኢቲቪ ከቀረቡ «የሕዝብ» አስተያየቶች አንዱ(የማታ ዜና፤ ታኅሳስ 29/2003)*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ በነጋዴውና በመንግሥት የአልጠግብ ባይነት አባዜ አጥንቱ አልፎ መቅኒው እየተነቀረ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ተወርቷል፤ተጽፎአልም። ግን እስከአሁን ምንም መፍትሔ አልተገኘለትም። በወያኔ ጊዜም ለዚህ ሥር የሰደደ ችግር ማርከሻ ይገኝለታል ተብሎ አይታለምም፡ ለምን ብለው ወደ ሥልጣን መጡና! ሀገርና ሕዝብ ለማደኸየትና ከነጭርሱ እርቃናቸውን ለማስኬድ መሆኑ መች ይዘነጋል?*

*ሰሞኑን ታዲያ ወዬ ሆዬ እንደለመደው በሕዝብ የልብ ትርታ ወጪ ትንሽ ቲያትር ቢጤ ማናፈስ አማረውና «ለጊዜው በ28 ዕቃዎች ላይ የመጨረሻ የመሸጫ ዋጋ ተመን አውጥቻለሁ፤ ከዚያ በላይ ንቅንቅ የሚል እንደ ግንቦት ሰባቱ የ97 ምርጫ ጣቱን እቆርጣለሁ. . . » አለንና በከንቱ ወስፋታችንን አላወሰው - እሱና ግብረ በላ ነጋዴዎቹ እያዋዙ በ20 ዓመታት ውስጥ ሰማየ ሰማያት ያደረሱትን ኑሮ በደቂቃዎች ውስጥ በዐዋጅ ለማውረድ። አስቂኝ መንግሥት። ሣቄን ለጥቂት በቅርቡ ጨረስኩ እንጂ እንከረከር ነበር።*

*በመሠረቱ ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ ቆንጆ ዐዋጅ ነው። ግን ጊዜያዊ እፎይታን ከመስጠት ዉጭ ምንም ፋይዳ የለውም፤ እደግመዋለሁ - እመኑኝ ቅንጣት ፋይዳ የለውም። የወያኔን የወረቀት ነብርነት ለመረዳት ብዙ መድከም አያስፈልግም። ለምሳሌ ባለፈው የተጋዳላይ ገብረ መድህን ጣያታዊ ሃውልት በ20 ቀናት ውስጥ እንደሚፈርስ ሲነገር ያኔ ቆትቤ ያስቀመጥኩዋት ትንሽዬ ሣቅ ቢጤ ነበረችኝና ከትከት ብዬ ነበር የሣቅሁት - በወያኔ ዘመን የማይሞከር ቅዠት መሆኑ ይታወቃልና። ለጊዜው ግን ለአንድ ወር ግድም «አሃ! ለ‹ንስ ዲሞክራሲ በሀገሪቱ አለ ፤ ለ‹ንስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፖለቲ‹ ነጻ የሆነ የሃይማኖት ተቋም አለ፤. . .» አስባለ። ቱሪናፋውም በዓለም ዙሪያ ናኘ። እኛም ልባችን ጦሽ እስኪል ሣቅን - ግን እስከአሁን አለን አንድዬን አይክፋው። የምንሞተው ኀሊናችን ጦሽ ሲል ነው። እሱ ደግሞ ያርጋል እንጂ መዋቲ ሥጋ የለውም።*

*በኅብላላው የደርግ ዘመነ መንግሥት ደርጊና ምን ዐወጀ አሉ - «ከዛሬ ጀምሮ አንድ ዕንቁላል ከአምስት ሣንቲም በላይ የምትሸቅጪ ትኖሪና እያንዳንድሽ ቀይ ሽብርሽን ከጎንሽ ታገኛታለሽ! ዋ! ሁዋላ ሁልሽ ጉድ እንዳትሆኚ!» ያኔ ነጋዴ ሆዬ ምን አለ ታዲያ - «እንዴ ድርግ አሽ‹‹ እንጂ መች ዕንቁላል ጣለ?» ዝርዝሩ አይጠቅምምና ወደዚያ አንሂድ - ትርፉ ቁጭት ነው።*

*አንድ ኪሎ ስ፯ር ተወደደ ተብሎ በብር 1.15ሣንቲም፣ አንድ ኪሎ ሥጋ በብር 5.00፣ ኩንታል ጤፍ ብር 50.00፣ ኪሎ ብርቱ‹ን በብር 0.50 ሣንቲም፣ኪሎ ክክ ምሥር በብር 1.50 (ምሥሩ እንኩዋን ነገረኛ ነው ይቅርብን ግዴለም) - ብቻ ምኑ ተወርቶ ኘ አቅሜ በሚፈቅደው መጠን እንዲሸጥልኝ እያደረገ በቅጡ ይገዛኝ የነበረ ኢትዮጵያዊ መንግሥት አሁን ‹ለው ስ፯ሩን በኪሎ ብር 17.00፣ ሥጋውን ብር 100.00 (ተመስጌን ነው አሁን ወደ 52 ሊወርድ መታቀዱ! ቂቂቂ) ፣ ብርቱ‹ኑን በኪሎ ብር 14.00፣ ምሥሩን በኪሎ ብር 22.00 (ጉድ በሉ እንግዲህ ጊዜው የጉድ ነው!) ከሚሸጥልኝ ሀገርንና ሕዝብን የ‹ደ የወሮበሎች ጥርቅም ይልቅ ሊወዳደሩ በማይችሉበት ሁኔታ ለኔ የሚሻለኝ የመጀመሪያው ነው - መቶ በመቶ። ምርጫ ደግሞ የግል እንጂ የወል ሊሆን አይጠበቅምና ማንም አፋን ሊያፍታታብኝ እንዳሞክር። ዴሞክራሲያዊ መፍቱን በሌላ*

ይለማመድ እንጂ በኔ በድሃው የኑሮ ቁስል እንቾት በመስደድ እንዳይሆን ይጠንቀቅ:: በኀሊናም በመንፈስም በአ‹ልም በርሃብም ብቻ በሁሉም የመግደያ መሣሪያዎች እያፈረጠ ሲችል በአንዴ ሲፈልገው ደግሞ በአዝጋሚ ሁኔታ(ያ ይበልጥ ስለሚያስደስተው) ከሚገድለኝ የጠላት ተላላኪ ምንደኛ ሠርጎ ገብ ይልቅ የኔው ነው የምለው ግን ጠባዩን ተረድቼ ወንበሩን የማልቀላውጥበት የራሴው መንግሥት አንቀጥቅጦ ይግዛኝ - አሁንም ይህ ምርጫ የራሴና የራሴ ብቻ ነው! በየትኛው ዕድሌ አግኝቸው እንጂ:: እንዴ? ደርግ እኮ ሥልጣኑን አትን‹በት እንጂ ወርቅ መንግሥት ነው:: እግዜርን መ‹ዱና ለሥልጣኑና ለሀገር አንድነት ሲል ሕዝብን መጨፍጨፉ ነው ወንጀለኛ ያደረገው:: ለክር ነው መመሥከር ኀበዝ! የሞተ ግንድ ምሣር ምናምን ሆኖ እንጂ በሃቅ እንነጋገር ከተባለ በኢትዮጵያዊነት የሀገር ፍቅር ስሜት ደርግን የሚስተ‹ከል የለም:: እነዚህን ጉዶችማ አደራችሁን ለውድድርም እንዳታቀርቡዋቸው፤ ማቅረቡ በራሱ ይሙት በቃ የሚያስፈርድ ወንጀል ነው:: አገር ሻጭና የሀገር ድንበር አስጠባቂ ለሀገር ፍቅር መለኪያ ፈተና በአንድ የፈተና አዳራሽ አይቀመጡም:: አይጥና ድመት? ጨለማና ብርሃን? እሳትና ጭድ? ምን ህብረት አላቸውና?

የወያኔን መንግሥት ያላወቁ ዜጎች አሁን ድረስ በደርግ ሲንገፈገፉ ይታያሉ:: እኔም የደርግን ዉድቀት እንዲያሳየኝ ፈጣሪን ያላስቸገርኩት የማስቸገር ዓይነት አልነበረም:: እንደሚመስለኝ የገባሁትን ስለት ሳልፈጽም በመቅረቴ ሳይሆን አይቀርም የባሰውን አውሬ መንግሥት እየው ብሎ የሰጠኝ:: አየሁት፤ የዱሮውንም አመሰገንኩ:: ደግሞም አልሁ - እኛ በር‹ቶች ኢትዮጵያውያን ያለፈውን እየናፈቅን - የአሁኑን እየጠላን - የወደፊቱን እየፈራን እንድንኖር አንዳች ሥውር ኃይል የፈረደብን የነዋሪዎች ሙታን ነን:: ይህ የውሳኔ ሃሳብ የማይስማማው አለመቀበል መብቱ ነው:: እኔ ግን ቀጠልኩ::

የአንድ ወቅት ምልከታ - ከልደታ እስከ መገናኛ ዐይን ቦታዎች ላይ ከተሠሩ 86 ሕንጻዎች መ‹ከል 83 የሚሆኑት የወያኔ ናቸው - የትግርኛ ተናጋሪ ወያኔዎች:: ቀሪዎቹ ሦስቱ ደግሞ ትግርኛ የማይናገሩ ሆዳም «ወያኔዎች» ንብረቶች ናቸው:: እነዚህ መናጆዎችም አስፈላጊነታቸው በሚቀዘቅዝ ጊዜ - መቀዝቀዙም የማይቀር ነው - ንብረታቸውን ወዲያው የሚነጠቁበት ቀይ ‹ርድ የተያዘላቸው ናቸው:: ዕድሜ ለመንግሥት ባንኮች - የነሱ አንዱ ግዳጅ ለወያኔ ትግሬዎች ያለመያዣ የፈለጉትን መጠን(እንደሁኔታው ሊመለስ የማይችል) ገንዘብ «ማበደር»ና ከዘረኛው ሥርዓት ሊያፈነግጡ የሚዳዳቸውን ሆዳሞች ደግሞ በሆነ ዕዳ እየያዙ ያፈሩትን ሀብትና ንብረት በመቀማት «እኔው እንዳከበርኩህ እኔው አደኸይሃለሁ» የሚለውን ወያኔያዊ ህገ ኦሪት ማስፈጸም ነው::

ሰሞነኛ ምልከታ - ከመገናኛ እስከ ሲኤምሲ በመንገዱ ዳርና ዳር እየተሠሩ ከሚገኙ እጅግ በር‹ታ ፎቆች በአንድ እጅ ጣቶች ከሚቆጠሩት እጅግ በጣም ጥቂቶች በስተቀር ከሞላ ጎደል ሁሉም ማለት በሚቻል ሁኔታ የትግርኛ ተናጋሪ ወያኔዎች ንብረቶች ናቸው:: ምድረ አበሻ ተንጨርጨሪ እንግዲህ - ምናባሽ ታመጫለሽ? ላንቺ የተመደበልሽ በራስሽ ቀየ የበይ ተመል‹ች ሆነሽ እነሱ በግሳትና በቁንጣን ሲሰቃዩ አንቺ በርሃብና በጥማጥ እየተሰቃየሽ እነሱን በአፕታይዘርነት ማገልገል ነው:: አለዚያም ጊዜ እስኪያልፍ ወጣ ብሎ ብርዱንና ቆፈኑን በስደት ማሳለፍ:: እነዚህ አዕምሮና ይሉኝታ የሚባል ነገር ያልፈጠረባቸው የትግሬው ገዢ መደብ አባላት ሀገሪቱን በክራንቻ ጥርሳቸው አጥንቷን ዘልቀው እየቦጠቦጡዋት ነው:: ሌላውም በድህነት እያለቀ ነው:: በዚህ ሁኔታ ላይ የሚገኙት ወያኔዎች ናቸው እግዲህ ለሕዝብ አዝነውና ተቆርቁረው የሰሞኑን የዋጋ ቅነሳ አዋጅ ያወጁት - የወቅቱ ፖለቲ‹ አንጼውኑ ጠርጣሪ አድርጎኛልና ይቺ ጎንበስ ጎንበስ ዕቃ ለማንሳት ነው እንደሚባለው የወያኔ ደርሶ ለሕዝብ ኣሳቢ መስሎ መቅረብ ለሆነች ዓላማ ሥኬት መሆን አለባት እንጂ ከሞትን በሁዋላ አለሁ ማለት የአትርሱን ያህል ነው:: ደግሞስ 52 ብር ከፍሎ ሥጋ የሚበላው ድሃ ሥንቱ ነው? ይሄ

ቅነሳ ነው ወይስ ቧልትና ቀልድ? ቀልዱ ለምን ለከት አይበጅለትም? ብዙዎቻችን ሥጋ መብላት ያቆምነው 100 ብር ሲገባ ሳይሆን 20 እና 25ትን ሲያልፍ መሆኑን ወያኔዎች አያውቁም ይሆን? ዳሩ የጠገበ የተራበን መች ያስታውስና!

ወደሌላ ነባር ምልከታ:: የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሞላ ጎደል ሁሉም የሥልጣን እርከኖች በማይማን የወያኔ ትግሬዎች(ልብ አድርጉልኝ 'የወያኔ ትግሬዎች' የምለው የኛ ም ትግሬዎች- ኢትዮጵያውያን ትግሬዎች ማለት ነው - ከኛም በበለጠ በንዴት እየበገኑ በትግሉም ከኛው ጋር መሰለፋቸውን ለማጠየቅ ነው) - እናም ልድገመው በማይማን የወያነ ሓርነት ትግራይ ጉጅለ ትግሬዎች መሞላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የዕዝ ሠንሰለት ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ በትግሬ ወያኔዎች መጠርነፉ እንዳለ ሆኖ፣ የሀገሪቱ አንኳር የጥቅም ቦታዎች ሁሉ (በዋናነት ንግዱና ፖለቲ‹ው) በወያኔ ትግሬዎች መያዙ  እንደተጠበቀ ሆኖ፣ «የኢኮኖሚውን ምሰሶ ያልያዘ ፖለቲ‹ውን አይዝም» ከሚል የብልጣ ብልጦች የቆዬ ፈሊጥ በመነሳት ሌላውን እያደኸዩ እነሱ ብቻ በሃብት ማማ ላይ አላግባብና በዘረፋ ፊጥ ማለታቸው የአደባባ ምሥጢር መሆኑ እንዳለ ሆኖ ፣ . . . የአዲስ አበባን ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ስብጥር ብናይ ከመቶ ተማሪዎች ከ65 - 70 የሚደርሱት ትግርኛ ተናጋሪዎች ናቸው:: በአዲስ አበባ ውስጥ በግል ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎችም አብዛኞቹ ተማሪዎች ጌቶቻችንና የጌቶቻችን ልጆች/ቤተሰቦች ናቸው:: ሌላውማ በምን አቅሙ? የልጆቹን ወስፋት መክላት ከአቆመም ዘመናት ተቆጠሩ:: ይህን ገሃድ እውነት የአዲስ አበባ አውራ ጎዳናዎችና ዘበኛ የሌላቸው በረንዳዎች በግልጽ የሚመሠክሩት አሳዛኝ ክስተት ነው:: በነገራችን ላይ የነሱ መማርና መክበር አይደለም የሚያበሳጨው፤ ያ ያስደስታል እንጂ አያስከፋም:: በነሱ መሠሪ ተንኮል ሀገርና ሌላው ቀና ሕዝብ በማይምነት ክርታስ መጋረዱና በድህነት አረንቋ መዘፈቁ ነው በቁጭት የሚያንገበግበው:: እንጂ የጋሪዮሽ የዜግነት መብታቸውን ተጠቅመው ለሁላችንም እኩል በተስተ‹ከለ የመወዳደሪያ መደላድል(የምርጫ ቅስቀሳ አስመሰልኩት ልበል?) ተወዳድረን የሕይወትን አቀበት ብንወጣማ ኖሮ አንዳችም ችግር አልነበረውም:: ያኔ የሚወድቀው ወድቆ እታች ሆኖ ቢያላዝን ሰሚ አያገኝም- በዕድሉ ይዘን እንጂ:: አሁን ግን ዕድል የለ፤ ሥራ የለ፤ ጉብዝና የለ፤ በትምህርት መግፋት ዋጋ የለው፤ ኢትዮጵያዊነት የለ፤(ጉዶቹ ይቺን የዱሮ ቃል ቀቅላችሁ ብሉዋት ይሉናል) ዘር ብቻ - ያውም ከ«ወርቁ» ዘር ትግሬና ትግሬ ሆኖ መፈጠር ብቻ!! (እንደማንኛውም የሰው ዘር ትግሬም ወርቅ ዘር ነው፤ የመለስ ቃል ስለሆነች ለጌታየ ዕውቅና ለመስጠት  ነው ምልክት ያደረግሁባት)  ታዲያ እኔ የመንጌ ልጅ ተንግዲህ በስተርጅና ምን ይዋጠኝ? ተመልሼ ወደ እናቴ ማሕጸን አልገባ ነገር የማይታሰብ ነው፤ እሱዋም ከሞተች ዓመታትን አስቆጠረች:: ዳሩ እኔም ልከተላት ምን ቀረኝ? በውነት ግን እኮ ከሞትን ቆየን:: አሁን ብዙዎቻችን ኢትዮጰያውያን እየኖርን ነው? በኢቲቪ ‹ልሆነ በስተቀር በተግባር ብዙዎቻችን መኖር አቁመናል እኮ:: እንዳንወሻሽና ጎሊናችን እንዳይታዘበን:: ዉስኪ ሲጠጡና ጮማ ሲቆርጡ የምናየው በኢቲቪ የሞኞች መስኮት እንጂ እኛማ ድንች እንኩዋን ባቅሙዋ ኮርታብን በኪሎ ስድስት ብር ስትገባ ሥጋና አረቂ እንዴት ይታሰባል፡ እነዚህ ባንድ ወቅት ለብዙዎቻችን ተራ የነበሩ ነገሮች አሁን አሁን በህልማችንም እንኳን መምጣት ‹ቆሙ ሰነበቱ:: ለእኛ ሥጋ ቅንጦት ነው - ማየትም አይፈቀድልንም ጌቶቼ አንባቢዎች:: እዬዬም ሲዳላ ነው አሉ? የምን ኑሮ ነው- የሲያሉን ከሆነ ልክ ነው አለንበት:: ያለ ገልማጭ ያለቆንጣጭ በነጻነት የምንገፋው ኑሮ እሱን ነው:: ገዢዎቻችንም ሲያላውያን መሆናቸውን ጥቂቶቻችንም ብንሆን እናውቃለን - ከምግባራቸውና ከሚጠብቃቸው መፃኢ የመጨረሻ ዕጣ ተነስተን ይህን የማየታበል ዘላለማዊ እውነት ማወቃችንን በኩራት እናውጃለን::

ይታያችሁ እንግዲህ ትግራይ አልበቃ ብላ በሁሉም ረገድ ያለው ያልተቋረጠ ወረራ ተፋፍሞ ቀጥሎኣል:: የሚማሩት፣ የሚነግዱት የሚሠሩት የሚሠርቁት የሚዘርፉት፣ የሚዘባነኑት፣ የሚያሳስሩት፣ የሚያስፈቱት፣ የሚገነቡት፣ የሚያፈርሱት፣ የሚያነዱት፣ የሚያከስሉት፣ የሚንጠባረሩት፣ አንገት የሚያስደፉት፣ የሚያዙት፣

የሚናዝዙት . . . እነሱና የነሱው ልጆች ናቸው:: የነዚህን ተቃራኒ የሚሆኑትና ምድርና ሰማይ የተደፋባቸው ደግሞ የኛ ልጆች ናቸው:: ወደን ነው! - እሰይ! ይበለን! 85 ሚሊዮን አባግዕ በጥቂት ተኩላዎች የሚበሉባት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ናት:: ለምን? አንድ ልብና አስሳሰብ የለንማ- እንዲኖረንም አንፈልግማ! ሁልጊዜ የከይሲዎች መሣሪያ መሆን ይቀናናላ! እናም እኛ እንጂ ሞኞች ሀገር አማን ብለን ተኝተን የምናድር ወያኔዎችማ ከመነሻው «ብልሆች» ናቸው - እንደንብ ተግተው ሌት ከቀን ማር ይሠራሉ፤ እነወዲ ተጋሩ ማሩዋን ለብቻቸው ይቆርጣሉ:: ለኛም ጭሱ ይተርፈናል እንጂ ተማሩ ሰፈፉ እንኳዋን አይደርሰንም:: እርግማን ነው:: መናደፍን በዋና መሣሪያነት ይዘው ይተገትጉናል:: ዕረፍት አያውቁም - የሲያል ትሎች፤ የገሃነም እቶን ትንታጎች! ግን ይተግትጉን ሲያንሰን ነው:: ዱሮውንም በሞኝ ደጃፍ ነው ማርና ሞፈር የሚቆረጠው::

ወያኔዎች የቼዝ ጨዋታም ያውቃሉ:: «እስቴፓቸውን» ጠብቀው እንደተጫወቱ እስከአሁን አሉ፤ ወደፊትም የመቶና ከዚያም በላይ ዕቅዳቸውን በብልሃትና በዘዴ ይተልማሉ:: በዚህ አያያዝም ይሳ‹ላቸዋል:: በተኙ ሰዎች ላይ ቁማር መቆመር እጅግ ቀላል ነገር ነውና:: ምቀኛ አበሻ ሁላ እንግዲህ ምን ይዋጥሽ? ገና ታሪያለሽ - ኣ ኣ - ታርሪያለሽ ይባልልኝ:: እነዚህ ድፍን ቅል ራሶች የሚሠሩት ትውልድን የማያቀባብር ሥራ ተወርቶ አያልቅም:: ይህን የፈጠጠ ነባራዊ እውነት ለመተንፈስ እንኳዋን አንችልም:: «እነገሌ ቢቀየሙንስ? እገሌ ቢያኮርፍስ . . .) እያልን ገዢዎቹ ባገኙት ዋጋ ቸርችረው በልተው የጨረሱትን ይሉኝታ አንግበንና ታቅፈን በይሉኝታ ታሥረን ቁጭ ብለናል:: እኔ እንደ ጥቂት ጓደኞቼ ቢያንስ ተናግሬ ወጣልኝ:: መስመሩን ለከፈቱልኝ ለነዚያ አይናቸውን ቀድመው ለገለጡ ወገኖቼ ያለኝን ውዴታና ፍቅር በዚህ አጋጣሚ እንድገልጥ ይፈቀድልኝ ዘንድ እመኛለሁ::

በመጨረሻም ወያኔ ትግሬዎች እንዲህ እንደሚሉኝ አውቃለሁ- ቢያንስ እገምታለሁ፤ « ግመሎቹ ጉዞኣቸውን ዉሾቹም ጩኸታቸውን ይቀጥላሉ»:: አዎ! እውነት ነው:: እኔም እላለሁ፤« ይዋል ይደር እክጂ አህያ የጅብ ናት» - ኪዩባ ‹ልሄደች:: ወያኔዎች ግን የትም መሄድ አይቻላቸውም:: ምክንያቱም የሠሩትና እየሠሩት የሚገኙት ወንጀልና በደል እንደ ቀላል ዕድፍ በእንዶድ አሊያም በሣሙና - (ሣሙና ሣሙና አንድ ነገር ትዝ አለኝ) - ከአዕምሮኣቸው በቀላሉ ታጥቦ የሚወጣ ነገር አይደለምና:: የነሱ ወንጀል የትም ቢሄዱ ያሳድዳቸዋል፤ ፍትህ ባይበየንባቸው እንኳዋን አንድ ቀን ወደፊት ይኖራቸዋል ተብሎ የሚጠበቀው አያ ኅሊና ፈጥርቆ ይይዛቸዋል:: ያኔ በመንፈስም በአ‹ልም እየሰለሉ(እየኮሰመኑ) ይሄዱና «አፈር ነበርክ ወዳፈርህ ትመለሳለህ» የተባለውን የመለኮት ሕግ ይረዳሉ:: ያኔ ባደረጉት ነገር ሁሉ ራሳቸውን ይዘው ያለቅሳሉ፤በጸጸት ጸጉራቸውን ይነጫሉ፤ ሊያውም ያንን ዕድልም ሊያገኙት ከቻሉ ነው:: ያኔ «ምነው ወያኔ ትግሬ ሆኜ ባልተፈጠርኩ!!» የሚባለው ነባር ትንግርት እውን ይሆንና እውነት ተገቢ ሥፍራዋን ትይዛለች - የተፈጠሩባትን ጠማማ ዕለትም ይራገማሉ፤ እንደ ኢዮብ - እሱ እንኳዋን አለአበሳው ለሰይጣን ፈተና አልንበረከክም በማለቱ ነው፤ እንደጥቂቶቻችን::

ከፍ ሲል ትዝ ወዳለኝ ነገር ልመለስ? ጊዜ አላችሁ? - አንድ ወቅት ወደ አንድ አ‹ባቢ ሄድኩና አንድ ዋናው የመግቢያ በር ብቻ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር መፍጀቱ በጉልህ የሚያስታውቅበት የተንጣለለ ግቢ አያለሁ:: የማን እንደሆነ ስጠይቅ በቁጥር የሚጠራ ሣሙና አምራች ፋብሪ‹ ባለቤት መሆኑን በአጠገቡ ተኮልኩለው የተቀመጡ ልጆች ነገሩኝ:: ነገሩን ሥር ለማስያዝ - እኔ የቻይና ኤምባሲን ፈልጌ ነበር ወደዚያ ቦታ የሄድኩት:: የምፈልገውን የኤምባሲውን ግቢ ሳላውቅ ንቄ ትቼ ያን የገነት በር ሳማትር የመጣሁበትን ጉዳይ በመንፈስ የተረዱልኝ የሚመስሉት ልጆች ምንም ሳልጠይቃቸውና ፍልጎቴንም ለማወቃቸው ቅንጣት ሳይጠራጠሩ፤« ጋሼ የቻይና ኤምባሲ ይሄኛው ነው!» አሉና በቂልነቴ እንድገረም አደረጉኝ:: «ኤምባሲውን መፈለጌን እንዴት

ዐወቃችሁ?»አልኩ - ለመማር፤ ከነዚያ ልጆች መሃል ሎብሳንግ ራምፓን መጠበቅ ያስቸግራላ! . . . የሆነው ሆኖ ያን ሣሙና አሁን የምንገዛው ከስድስት ብር በላይ ነው። እኛ ለሱ እየሞትን እሱና መሰል ቀፎ ራስ ነጋዴ አጋሚዶች ወሮበላው ትግሬ መንግሥት ባመቻቸላቸው የብላ ተባላ ዓሣማዊ ሥርዓት እየፈጁን ነው። አያ የሣሙናው ነጋዴ ይቅርታ እንዲያው በነገር መሃል ተሰንቅሮ ታውሶኝ እንጂ አነሳሴ ለዚያ አይደለም፤ ወደፊት ባይሆን - ኢንሻአላህ - በሰፊው ልንወያይ እንችላለን።